

<u>በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።</u>

ለርዕሰ አድባራት ለንደን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን

መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት በሙሉ

ከዶ/ር በቀለ ገሠሠ (ታህሣስ ፳፯ ቀን ፳፻፩ ዓ/ም)

ለምወዳችሁና ለማከብራችሁ መንበረ ካህናትና ምእመናን በሙሉ፤

ቸሩ አምላካችን ዛሬ ዓለማችን አጅግ በጣም በተናጋችበት፤ በታወከችበት እና በተናወጠችበት ወቅት ጠብቆ ደግፎ አስካሁን ስላደረሰን ታላቅ ምስጋና ይግባዉ።

ይህቺን ትንሽ ማስታወሻ አንድጽፍ የተገደድኩት ምንም አዲስ ነገር ለመጨመር ሳይሆን በዚህ አካባቢ በነበረኝ የረዥም ጊዜ ተሞክሮ ላይ በመመርኮዝ ለነባሮች ማስታወሻ፤ ላዲሶቹ ደግሞ የዐቅሜን ያህል ግንዛቤ ለማስጨበጥ እና በቤተ ክርስቲያናችን ዉስጥ ሰላም እንዲሰፍን የግሌን ትንሽ አስተዋጽኦ ለማድረግ ስለሆነ በጥሞና አንድትገነዘቡልኝ ዝቅ ብዬ አለምናለሁኝ።

፩ኛ/ <u>በመተዳደሪያ ደንብ ምክንያት ወይም ሰበብ የቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና ኅልዉና መናጋት የለበትም።</u>

ማንኛዉም ተቋም የሚመራዉ በሕግና በመተዳደሪያ ደንብ ነዉ። ቤተ ክርስቲያናችን ለረዥም ጊዜያት የዳበረ የራሷ ሥርዓተ ኅይማኖትና ቀኖና አላት። መተዳደሪያ ደንቦችም እንደዚሁ እንደየአስፈላጊነታቸዉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተረቀቁና እየተሻሻሉ ሲያገለግሉ ኖረዋል። ዛሬ ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ? የዉስጥ መተዳደሪያ ደንባችንን አሻሽሉ ረቂቁን የሚያቀርብ ኮሚቴ በሰበካዉ መንፈሳዊ ጉባኤ ተሰየመ። ረቂቁን በጥሞና ሰምቶ ጥያቄና አስተያየት አቅርቦ የማያስፈልገዉን ማስቀረት፤ የጎደለዉን መሙላትና የሚጠቅመዉን በምስጋና ተቀብሎ ወደፊት መሄድ ሲገባ ሁካታና ሽብር ለምን አስፈለገ? እግዚአብሔርስ ይወደዋል ወይ? “የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ።” (መጽ. ምሳሌ፤1፤ 7-8)

እነሆ ዛሬ አንደምንመለከተዉ ግን፤ በቤተ ክርስቲያናችን ዉስጥ በሰላም ምትክ ሁካታ፤ በፍቅር ፈንታ የመረረ ጥላቻ ይታያል። አንዳንድ የሚሰሙ ቃላት ለጆሮ የሚቀፉ ሆነዉ ተገኝተዋል። በተከበረች ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ዉስጥ ስድብ፤ ድብድብና ዛቻ ፈጽሞ ቦታ የላቸዉም። “በአንድ ልብ ሆናችሁ በአንድ አፍ እግዚአብሔርን፤ እርሱም የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፤ ታከብሩ ዘንድ የትዕግሥትና የመጽናናት አምላክ፤ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ መሆንን ይስጣችሁ።” (የሐዋርያዉ የጳዉሎስ መለክት ወደ ሮሜ ሰዎች፤ 15፤ 5-6) የሚለዉን ጠቃሚ ትምህርት አንርሳ!!

**ቸሩ አምላካችን ልቦና ይስጠን፤** “አቤቱ አድነኝ ደግ ሰው አልቆአልና፤ እርስ በርሳቸው ከንቱ ነገርን ይናገራሉ፤ በሽንገላ ከንፈር ሁለት ልብ ሆነው ይናገራሉ። የሽንገላን ከንፈሮች ሁሉ እግዚአብሔር ያጠፉቸዋል።” (መዝ. ዳዊት፤ 11፤1-3)። እንኳንስ በተቀደሰች ቤተ ክርስቲያን ዉስጥ ይቅርና በመንገድ ላይ እንኳን በወንጀል ያስጠይቃል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የፀሎት፤ የሰላም፤ የፍቅር፤ የመቻቻያ እና ይቅር መባባያ መድረክ ናት እንጂ የሽብር ቦታ አይደለችም። “ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛዉን ደግሞ አዙርለት” (ሉቃ. 15፤ 4-5) የሚለዉን ትምህርት እንዴት እንርሳ? “እርስ በርሳችን እንዋደድ፤ ፍቅር የሌለዉ እግዚአብሔርን አያዉቅም፤እግዚአብሔር ፍቅር ነዉና” (መጀመሪያይቱ የሐዋርያዉ ዮሐንስ መለክት 4፤ 8-9)

ሰዎች ነንና እያንዳንዳችን ድክመቶች ይኖሩናል፤ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምንገባዉ ግን ኅጢአታችንና ድክመታችንን ወደኋላ አድርገን ፀልየን ለምነን የእግዚአብሔርን ይቅርታና በረከት ልንቀበል እንጂ ኃጢአታችንን





ለማባባስ አይደለም። “በወንድምህ ዓይን ያለዉን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፤ በራስህ ዓይን ግን ያለዉን ምሰሶ ስለምን አትመለከትም? ... አንተ ግብዝ፤ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶዉን አዉጣ፤ ከዚያ በኋል በወንድምህ ዓይን ያለዉን ጉድፍ ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ” (ሉቃ፤ 6፤ 39-42)

፪ኛ/ ያለፉት ችግሮቻችንና መፍትሔዎቻቸው

ከ30 ዓመት በፊት እጅግ በጣም የምንወዳቸውና የምናከብራቸው አባታችን አባ አረጋዊ ወልደ ገብርዔል (በኋላ ብጹዕ አቡነ ዮሐንስ) መጥተው ይህቺን ቤተ ክርስቲያን አክተን በሚባል ቦታ በለንደን ውስጥ መሰረቱ። በወቅቱ በእንግሊዝ አገር የኢቲዮጵያውያን ሰደተኞች ቁጥር እምብዛም ስላልነበረ የመጀመሪያ አመጣጣቸዉ በካሪቢያዉያን ወንደሞቻችንና እህቶቻችን ጥያቄ ነበረ። እነዚህን ወገኖቻችንን አጠመቁ፤ አስተማሩ፤ የቤት ክርስቲያን ሀይማኖታዊ አገልግሎት በመስጠት እጅግ ታላቅ የሐዋሪያ ተግባር ፈፀሙ። ቀስ በቀስ የኢተዮጵያውያን ቁጥር እየጨመረ መጣ። በቋንቋ እና በተመሳሳይ ልዩነቶች ምክንያት የተነሳ በኢትዮጵያውያንና በካሪቢያን ወገኖቻችን መሀከል ታላቅ ግጭት ተፈጠረ። በአባታችንም ላይ ብዙ ጉዳት ደረሰ። ግጭቱ ከዐቅም በላይ ሆኖ ስለተገኘ ብፁዕ አባታችን አክተንን ጥለው ወደ ቤይዝ ዋተር ዞረው ቅዱስ ማቴዎስ ከሚባለው የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ አንዱን ክፍል በመያዝ መንፈሳዊ አገልገሎቱን ቀጠሉ። ከጊዜ ወደ ጊዜ የካህናትና የምእመናን ቁጥር እየጨመረ ስለመጣ ሰፋ ያለ ቦታ በማግኘት ቤተ ክርስቲያናችንን ወደ ግሪን ፓርክ አዞሯት። በዚያ ቦታ ቤተ ክርስቲያናችንን ከገጠሟት ዋና ችግሮች አንዱ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርኩን የለንደን ጉብኝት ተከትሎ የተነሳዉ ታላቅ ሁካታና ክፍፍል ነበር። ሆኖም ግን ቀስ በቀስ በብዙ ብርታትና በእግዚአብሔር ቸርነት ሰላም ወርዶ መንፈሳዊው ግልጋሎት ቀጠለ። በዚህ ቦታ እንዳለን ፍጹም ጤነኛ የነበሩት ብፁዕ አባታችን አቡነ ዮሐንስ ምንም ሳይታመሙ እጅግ አስደንጋጭ በሆነ መልክ በድንገት ተለዩን። ልዩ አባትና ሐዋሪያ ነበሩ። “እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፤ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል” (ዮሐ፤ 13፤14) የተባለዉን የጌታ ቃል ሙሉ በሙሉ በመከተል ዝቅ ብለው እግሮቻችንን አጠቡ፤ አጠመቁ፤ አስተማሩ፤ ባረኩ፤ ላገሩ ባዕድ ነኝ ሳይሉ እየዞሩ የታመመዉን ሁሉ ጠየቁ። “መቶ በግ ያለዉ ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋዉን እስኪያገኘዉ ድረስ ሊፈልገዉ የማይሄድ ከእናንተ ማን ነዉ?” (ሉቃ፤ 15፤ 4-5) የሚለዉን ቃል በመከተል ባንዳንድ ምክኒያቶች አኩርፈው ከቤተ ክርስቲያን የተገለሉትን ወገኖች ሺማግሌ በመላክና በማስለመን ወደ ቅድስት ቤታቸዉ መለሷቸዉ፤ ሙሉ መንፈሳዊ አገልግሎት በብቃት አደረሱ። ከእኚህ ብፁዕ እና ውድ አባታችን ብዙ መማር ይገባናል።

ከዚያም በኋላ በተለያዩ ጊዜያት አያለ ፈተናዎች ገጥመውናል። የዋና ዋና ችግሮች ምንጭ የቤተ ክርስቲያኗን የዉስጥ አስተዳደርና መተዳደሪያ ደንብን በተመለከቱ ጠያቄዎች ዙሪያ ነበር። እዚያው ግሪን ፓርክ በነበርንበት ባንደኛው ወቅት አንድ ካህን ካልቅድመ ማስጠንቀቂያ በድንገት ከች አሉ፤ በሹመትና ሽረት ዙሪያ ያልተጠበቀ ውዝግብ ተፈጠረ፤ ስምምነት ጠፋ። በዳግመ ትንሣኤ ዕለት ጭራሹን የቤተ ክርስቲይያችንን ዋና በር ቁልፍ አስቀይረው አሸገው ዘወር አሉ። መግቢያ ስናጣ ካህናትና ምእመናን ተጉዘን በግርን ፓርክ በዛፍ ሥር በትልቅ ዝናብ ውስጥ ቆመን ስናስቀድስ ከአባቶችና እናቶች ዓይን ይጎርፍ የነበረው እንባ ምን ጊዜም አይረሳም። ከዚያም በኋላ በተለያዩ ጊዜያት በተለይ በካህናት መካከል በሥልጣንና ክፍያ ዙሪያ በተነሱ የከረሩ ግጭቶች ምክንያት ብዙ ፈተናዎች ዐይተናል። እታች ባጭሩ እንደተመለከተው፤ ጠንከር ያሉ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤያት በማቋቋም፤ መተዳደሪያ ደንብ በመንደፍ፤ የሰላም ኮሚቴ በመሰየም፤ መንበረ ካህናትንና ምእመናንን በማቀራረብ፤ በፀሎትና በእግዚአብሔር ኃይል እነዚህንም ችግሮች እየቀረፍንና እያስተካከልን እስካሁን ደርሰናል። ቸሩ አመላካችን ምስጋና ይግባው።

፫ኛ/ የቃለ አዋዲ ሚና

በቤተ ክርስቲያናችን አመራርና አስተዳደር ውስጥ ቃለ አዋዲ ዋናዉን ስፍራን ሚና ይይዛል። ቃለ አዋዲ በታላላቅ የእቲዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተዘጋጅቶ፤ በቅዱስ ሲኖዶስ ፀድቆ ሲያገለግል የቆየ የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ነው። የእኛም ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የእቲዮጵያ ኦርቶዶክስ



ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አካል ሆና በእንግሊዝ አገር የተመሰረተች እንደመሆኗ መጠን በቃለ አዋዲው ላይ የተመሰረተ የውስጥ መተዳደሪያ ደንበ አረቅቃ፡አስፀድቃ እስካሁን ስታገለግል ቆይታለች። በመሆኑም የእቲዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ኃይማኖትንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ትከተላለች። መላው መንበረ ካህናትና ምእመናን ያካተተ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መስርታለች፤ ይህ ጠቅላላ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስመራጭ ኮሚቴ በመሰየም የዕለት ተዕለት የቤተ ክርስቲያኗን ተግባራት የሚከታተልና የሚያስፈጥም የአገልግሎት ዘመኑ 3 ዓመት የሆነ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤን ይመርጣል። የሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በደመዎዝ፤ በአበል ወይንም በነፃ የሚያገለግሉ ካህናትን መርጦ፤ በሰበካው መንፈሳዊ ጉባኤ አስፀድቆ ያሠራል፤ ገንዘብና ንብረትን ይቆጣጠራል፤ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያኗን ተግባራት ይፈጽሙ ዘንድ ንዑሳን ኮሚቴውዎን ያቋቁማል (ለምሣሌ፤ የካህናት አስተዳድር፤ የትምህርት ዘርፍ/ ሰንበት ት/ቤት፤የልማት ዘርፍ፤ የገንዘብና የንብረት ዘርፍ፤ የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ማደሻ፤ የሕሣብ ዘርፍ)። በተጨማሪም ልዩ የሰላም ኮሚቴ ተመስርቶ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

፩ኛ/ ተጨማሪ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ለምን አስፈለገ?

ቃለ አዋዲ በዋናው የተዘጋጀው በኢትዮጵያ ውስጥ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት መተዳደሪያ እንደመሆኑ መጠን፤ በተለይ የአብያተ ክርስቲያናትን ገንዘብና ንብረት ጥበቃ በተመለከተ ደንቡ የተመሰረተው በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሕግጋት ላይ እንደመሆኑ መጠን ከኢትዮጵያ ውጪ ሙሉ በሙሉ ተግባር ላይ እንዳይውል የሚገድቡት ጉዳዮች አሉ። እላይ ባጭሩ ለመግለጽ እንደሞከርኩት፤ ቤት ክርስቲያናችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሰ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነቷን ሙሉ በሙሉ በተግባር ላይ እያዋለች፤ ነገር ግን በተለይ የገንዘብና ንብረት ጥበቃን በተመለከተ የግድ ማሟላት የሚገቧት መንግሥታዊ መስፈርቶችና ግዳጆች አሉ።

ሀ) <u>የእንግሊዝ ቻሪቲ ኮሚሽን ምዝገባ ለምን አስፈለግ?</u>

በእንግሊዝ አገር ሕግ አበያተ ክርስቲያናት የሚመደቡት እንደ ምግባር ሠናይ ድርጅቶች ነው፤ ስለሆነም በእንግሊዝ ቻሪቲ ኮሚሽን ሥር መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ግዳጅ መሰረት ብፁዕ አባታችን አባ አረጋዊ (በኋላ አቡነ ዮሐንስ) ወደዚህ አገር መጥተው የእኛን ቤተ ክርስቲያን ከመሰረቷት ጊዜ ጀምሮ በእንግሊዝ ቻሪቲ ኮሚሽን ሥር ተመዝግባ ስታገለግል እስካሁን ድረስ ቆይታለች። እላይ እንደተገለጸው ባንድ በኩል የቻሪቲ ኮሚሽንን ግዴታ ለመወጣት በትረስት ዲድ/ቻሪቲ ኮሚሽን ስትመዘገብ፤ በሌላው በኩል ደግሞ ቃለ አዋዲውን ዋና መመሪያች አድርጋለች።

እነዚህ ሁለቱ (ማለት፤ ቃለ አዋዲያችንና የቻሪቲ ኮሚሽን) መተዳደሪያ ደንቦች እርስ በርሳቸው እንዳይጋጩ በቃለ አዋዲ ላይ የተመሰረተ አንድ ወጥ የሆነ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅተን እስካሁን ድረስ በሰላም ስንገለገልበት ቆይተናል።

ለ) <u>ካምፓኒ ሊሚትድ ባይ ጋራንቲ የሚለውስ ጥያቄ?</u>

ዛሬ ግን አዲስ ነገር ሆኖ እንደ ማወዛገቢያ ነጥብ የተወሰደ ነገር ቢኖር በእግዚአብሔር ፈቃድ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያናችን ተገዝቶ ክፍያው አልቆ የግላችን ንብረት ከሆነ በኋላ "ኃላፊነቱ የተወሰነ ድርጅት (<u>ካምፓኒ ሊሚትድ ባይ ጋራንቲ)</u> ተጨማሪ ፈቃድ መውጣት ይኖርበታል የሚለው ጥያቄ አካባቢ ነው። ይሄስ ጥያቄ እኛን እርስ በርሳችን ሊያፋጀን፤ ሊያባላን፤ ሊከፋፍለንና ጎልውናችንን ሊያናጋ ከቶ አይገባውም። ለምን አስፈለገ? ለሚለው ጥያቄ በንፁሕ ልቦና ቁጭ ብለን መወያየት እንችላለን። ሌሎች በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ያሉት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እንደግዳጅ የተቀበሉት ነው ወይ? ብሎ ጥናት ማድረግ ይቻላል። ከ1.6 ሚሊዮን ፓውንድ በላይ የፈጀ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በእጃችን ይገኛል። በተጨማሪም፤ የምእመናን ቁጥር ብዙ ነው፤ በየ ዓመቱ ከሙዳየ ምጽዋት፤ ከተጨማሪ መዋጮ፤ ከግልጋሎት ክፍያዎችና ከቁሳቁሶች ሺያጭ ብዙ የገንዘብ ገቢ ይሰበሰባል። ለዚህ ሁሉ ንብረትና ገንዘብ ባገሪቱ ሕግ መሰረት ኃላፊነቱ በማን እጅ መዉደቅ ይገባዋል? - በጥቂት ግለሰቦች ወይንስ በራሷ በቤተ ክርስቲያኗ? በሚሉት ጥያቄዎች ላይ በጨዋ፤ በሰለጠነና ክርስቲያናዊ በሆነ መንገድ ተነጋግረን መዉሰድ እሚገባን ምርጫ እና ስምምነት ላይ መድረስ እንችላለን።



## ፯ኛ/ <u>መደምደሚያ</u>

አብዛኞቻችን ለዚህች ዕለት የደረስነው በእመቤታችን አማላጅነተና በቸሩ አምላካችን ተዓምራዊ ችሮታ በቻ ነው። በስደት ጎዳና እጅግ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ወገኖቻችን በሱዳንና በሊቢያ በረሃዎች ላይ ወድቀው ቀርተዋል፤ ስንቶች በኬኒያ፤ በሞዛምቢክ፤ በደቡብ አፍሪቃ ረዥም ጎዳኖች ላይ ቀርተዋል፤ ስንቶች በሰሜን አፍሪቃና በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ተደብድበዋል፤ እንደባርነት ተገዝተዋል፤ ተደፍረዋል፤ ተገድለዋል፤ ራሳቸዉን አጥፍተዋል። ይህ ሁሉ እንግልት ሳይደርስበት በሰላምና በጤና እዚህ አገር የደረሰ ዜጋ ቁጥር እጅግ በጣም ጥቂት ነው። እዚህም ከደረስን በኋል የየዕለቱ ዜና መርዶ ብቻ ነው። በቁም የምንታይ መዉታን እንመስላለን። ምልክቶቹንም ለማየት ለቻለ ሁሉ የዓለም ፍጻሜ ራሱ መቃረቡን ማስተዋል አያዳግትም። በቅንጦት የምንኖር አይደለንም። እዚህም እንኳን ከመሀላችን ሆነው በጸሎት፤ በሰላም ኮሚቴ፤ በሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ፍለጋ እና በተለያዩ መንገዶች ከፍተኛ ግልጋሎት የሰጡ ብዙ የተወደዱና የተከበሩ ካህናት፤አባቶቻችን፤ እናቶቻችን፤ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በድንገት ተለይተውናል፤ እግዚአብሔር ብድራቸውን ይክፈልልን፤ ነፍሳቸውን ይማርልን፤ በመንግሥተ ሰማያት ያኑርልን፤ አሜን።

ከቦታ ቦታ ስንንከራተትና ስንጉላላ ብዙ ዓመታት አሳልፈናል። በስንት ፀሎት፤ ልቅሶና ጥረት ይኽን ቤተ ክርስቲያን እንዳገኘን ከእኔ ጋር የነበራችሁ ወገኖች ታስታውሳላችሁ። በድሆች ስደተኞች ምእመናን የ30 ዓመት በላይ የገንዘብ መዋጮና በቸሩ አምላካችን ፈቃድ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ በእጃችን ገብቷል። ባሁኑ ሰዓት በሰላም በፍቅር ባንድ ላይ ሆነን እየፀለይን ልጆቻችንን በቤተ ክርስቲያናዊ መንገድ ማሳደግ እና እርስ በርሳችን የምንደጋገፍበትና ላገራችን የምንፀልይበት ወቅት መሆን ይገባዋል። በመተዳደሪያ ደንብ ምክንያት ይኽን የሚያህል የሚያሳዝንና እጅግ በጣም የሚያሳፍር ግጭት ሊፈጠር አይገባም።

### ሀ) <u>ለካህናት አባቶቼ፡</u>

መጽሐፉን ከሁላችን በላይ ታቃላችሁ፤ የመጽሐፉ ቃል በትክክል በተግባር ላይ እንዲዉል ማስተማር ብቻ ሳይሆን መሳሌ ሆኖ መገኘት እንደሚያስፈልግ ብጠቁም እንደድፍረት እንዳይቆጠርብኝ እለምናለሁ፤ በርቱልን፤ የሰላም ጎዳና ጥረጉልን፤ ፀሎት፤ምህላ፤ሱባኤ ያስፈልገናል። ወቅቱ እጅግ አስጨናቂ መሆኑን ታቃላችሁና።

### ለ) <u>ለሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ፤</u>

በደንባችን መጠን የአንድ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የአገልገሎት ዘመን 3 ዓመት ነው። ያሆኑ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ግን ከደንባችን ውጪ ከሁለት ጊዜ በላይ በተከታታይ በሥራ ላይ ቆይቷል፤ አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ ሰላም በተናጋበት ወቅት ወይ የመተዳደሪያዉን ደንብ ጥያቄ እልባት ላይ ሳያደርስ፤ ወይም ተተኪ አባላት ሳያስመርጥ አንዳንድ አባላቱ ገሸሽ ማለታቸዉ ፍፁም ተገቢ አይመስለኝም። እስካሁን ላደረጉት መልካም አስተዋጽኦ እግዚአብሔር ብድራቸዉን ይክፈላቸው እያልኩ አሁን ከገባንበት ታላቅ ጣጣ እንወጣ ዘንድ በተለይ ከነርሱ ብዙ አስተዋጽኦ እንደሚያስፈልግ ጨምሬ ላሳስብ እወዳለሁ። ብዙውን ጊዜ ሴይጣን ጣልቃ ገብቶ ሁከት የሚባባሰው ሥርዓት ሲጠፋ/ሲጣስ፤ አመራር ሲደክም እና እምነት ሲላላ ስለሆን አስተዳደርንና አመራር ማጠናከር የግድ ይጠበቃል።

### ሐ) ለምእመናን ወገኖቼ በሙሉ፡

አትደንግጡ፤ አትበርግጉ፤ በፀሎትና በትዕግሥት የማይሆን ነገር የለም። ቡድን አትለዩ፤ የቸሩ አባታችን ቤት የተባረከ ነው፤ የሁላችንም እኩል ቤት ነው። እንበርታ፤ ለሰላም እንፀልይ። ንስሐ እንግባ።

## ቸሩ አምላክችን ከሁላችን ጋር ሁኖ መልካም ምኞታችንን ያሳካልን፤ አሜን።

